# አንበሳ ጫማአክሰዮን ማህበር ለተደረገለት የቴክኖሎጂ ድጋፍ ምስጋና አቀረበ፡፡

አዲስ አበባ ህዳር 2008፡ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በኢንቨሰትመንት፣ በምርትና ምርታማነት እና በግብይት የተለያዩ ድጋፎችን በማስጠት በቆዳ እና ቆዳ ዉጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ፋብሪካዎች ዉጤታማእና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማስራት ላይ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ዘመናዊ እና በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የሀብት አያያዝ እና አጠቃቀም ስርዓት (ኢንተርፕራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ ERP) በኢንስቲትዩቱ ዉስጥ ተግባራዊ ከማድረጉም ባሻገር የንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎችም ይህን ሰርዓት እንዲጠቀሙ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

በዚህ ረገድ አንበሳ ጫማአክስዮን ማህበር ዘመናዊ በሆነ መልኩ የሚደጃ ልውውጡን የተሳለጠ ለማድረግ በግሉ ከሚያደርገዉ ጥረት ጎን ለጎን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሊጂ በሚታገዝ የግብዓት አያያዝ ፣ የምርት አሜራረትና የምርት ዉጤቶችን ለዉጭ ሀገርና ለሀገር ዉስጥ ገበያ ለማስራጨት የኢንተር ፕራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ ስርዓትን ለማዘርጋት እንዲችል በኢንስቲትዩቱ በኩል የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎለታል፡፡

ስርዓቱም ከህዳር 12 ቀን 2008 ዓም ጀምሮ የሙከራ ትግበራ በፋብሪካዉ የጀሚረ ሲሆን ፋብሪካዉም ወደ እዚህ ስርዓት እንዲገባ በኢንስቲትዩቱ ለተደረገለት ድጋፍ በቁጥር አጫፋ/13/2.9 በቀን 24/03/2008 በፃፈዉ ደብዳቤ ምስጋናዉን አቅርቧል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማሳል የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች በሌሎች ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ የሚሰጠዉን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

# አንበሳ ጫማ አ/ማ

# Anbessa Shoe Share Co.

ስልክ) Tel.) 011-2751605,011-2754269,011-2754271 | ፖ.ሣ.ቁ.) P.O.Box) 1641 | ፋክስ) Fax ) 251-011-2756335 | E-mail:anbesss@ethionet.et www.anbessashoe.com.et


ቁጥር Ref. ኦሰ፪፬/13/2ዐ9

ቀን Date 24 ህዳር 2008

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የERP አገልግሎት የቴክኒክ እገዛ ምስጋና ስለማቅረብ

አንበሳ ጫማ አክስዮን ማህበር በጫማው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በመሰማራት ለረዥም አመት የካበተ ልምድ ያለው ሲሆን የደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት በተለያዩ ጊዜያት አዳዲስ ዲዛይኖችን በመስራትና ወደ ገበያው በማስገባት ምርቶቹን ዘመናዊና ምቹ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ከምርቶቹም በጥቂቱ ሲታይ የሲቪል ጫማዎች፣ የስራ ጫማዎች፣ የፖሊስ ጫማዎች እና የወታደር ጫማዎችን እያመረተ ለውጭ ሀገር እና ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የስራውን እንቅስቃሴና የተደረጉ ጥረቶችን ለማስቀጠል ድርጅቱ ዘመናዊ በሆነ መልኩ የመረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምና የመረጃ ልውውጡን የተሳለጠ ለማድረግ በየጊዜው በግሉ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ድርጅቱ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ የግብዓት አያያዝ፣ የምርት አመራረት እና የምርት ውጤቶችን ለውጭ ሀገርና ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማሰራጨት የኢንተርፕራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ (ERP) ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚያስገድድበት ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑና ድርጅቱም መጠቀሙ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት በኢንስቲትዩቱ በኩል የቴክኒክ እገዛ ተደርጎልን ሲስተሙ ከህዳር 12 ቀን 2008ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት መረጃዎችን በማስገባት (ሙከራ ላይ) የምንገኝ ሲሆን ችግሮች ቢከሰቱና ተጨማሪ ስልጠናዎች ቢያስፈልጉ እገዛ እንደሚደረግልን ታሳቢ በማድረግ እስካሁን ለተደረገልን እገዛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ባምላኩ ደምሴ
Bamlaku Demisse
ዋና ሥራ አስኪያጅ
General Manager

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መዝገብ ቤት
የማህደር ቁጥር 021-8-3/32-11
የደረሰበት ቀን 27/03/08
የተመራበት ቀን 27/03/08